# መመሪያ ቁጥር 02 /2014

## በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቢሮ የመምህራንና የትምህርት ቤት አመራሮች **የዲሲፕሊን አፈጻጸም ሥርዓት፤**

------2014ዓ.ም

ባህርዳር

# መመሪያ ቁጥር02/2014.

# በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቢሮ የመምህራንና የትምህርት ቤት አመራሮች የዲሲፕሊን አፈጻጸም ሥርዓት፤

በክልሉ ትምህርት ቢሮ በቅድመ አንደኛ ደረጃ ፣ በአንደኛ ደረጃ ፣ በመካከለኛ ደረጃ እና በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በመሥራት ላይ ያሉ መምህራንና የትምህርት ቤት አመራሮች የሥራ ባህሪ ከሌሎች የመንግሥት ሠራተኞች የተለየ በመሆኑ **የዲሲፕሊን አፈፃፀም መመሪያውንና የአሠራር ሥርዓቱን ከሙያው ጋር የሚጣጣም ማድረግ በማስፈለጉ፤**

ትምህርት ቤቶች የነገ ሀገር ተረካቢ ህፃናት በእውቀትና በመልካም ሥነ-ምግባር እየተኮተኮቱ የሚያድጉባቸው ተቋማት እንዲሆኑ ለማድረግ አስተዋጽኦ እንደሚኖረው በመታመኑ፤

# የቀጠለ

በትምህርት ቤቶች የሚስተናገዱ መምህራንና የትምህርት ቤት አመራሮች **ሠለማዊ የመማር ማስተማር ተግባር** ለማከናወን ይችሉዘንድ ሁሉም ለህግ ተገዥና በመልካም ሥነ-ምግባር የታነፁ እንዲሆኑ ማድረግ ተገቢ ሁኖ በመገኘቱ፤

የተቀመጠውን ሕግና የአሠራር ሥርዓት መሠረት በማድረግ ሃላፊነታቸውን በማይወጡ ላይ **ተቋማዊ እርምጃ መውሰድ** የሚያስችል የዲስፕሊን አፈፃጸም ሥርዓት መዘርጋት ስለታመነበት፤

የክልሉ ትምህርት ቢሮ በክልሉ አስፈጻሚ አካላት እንደገና ማቋቋሚያና ሥልጣንና ተግባራት መወሰኛ አዋጅ ቁጥር 280/2014 አንቀጽ 26(25) በተሠጠው ስልጣን መሠረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል።

## 1. አጭር ርዕሰ

ይህ መመሪያ **"የመምህራንና የትምህርት ቤት አመራሮች የዲሲፕሊን አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 02/2014 ዓ.ም"** ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## 2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ ፣

(1) **"ቢሮ"** ማለት የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የትምህርት ቢሮ ነው፤

**(2) "መምህር"** ማለት ከመንግሥት መምህራን ትምህርት ኮሌጆች እና ከመንግሥት ዩንቨርስቲዎች **በመደበኛው ወይም በማታው ወይም በክረምት** መርሃ ግብር በመምህርነት ሙያ ሥልጠና በመከታተል በሰርተፊኬት፣ በዲፕሎማ ወይም በዲግሪ የትምህርት ደረጃ ተመርቆ ቅጥር ወይም ምደባ የሚፈጸምለት ሰው ነው፤

**(3)“ርዕሰ መምህር”** ማለት አንድን ትምህርት ቤት በበላይነት የሚመራና የሚያስተዳድር ኃላፊ ነው፤

**(4)“ምክትል ርዕሰ መምህር”** ማለት አንድን ትምህርት ቤት በምክትል ኃላፊነት እንዲመራና እንዲያስተዳድር የተመደበ ኃላፊ ነው።

**(5)“ሱፐርቫይዘር”** ማለት የተጎዳኙ ትምህርት ቤቶችን በመደገፍና በማስተባበር ተቋማዊ ለውጥ እንዲመጣ የሚያደርግ የትምህርት አመራር ነው፤

**(6)“የትምህርት ቤት አመራር”** ማለት የቅድመ አንደኛ ደረጃ፣ የመጀመሪያ ደረጃ፣ የመካከለኛ ደረጃ ወይም የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችን በዋና ወይም በምክትል ኃላፊነት የሚመራ የሚደግፍና እና የሚያስተባብር ርዕሰ-መምህር ወይም ምክትል ርዕሰ-መምህር ወይም ሱፐርቫይዘር ነው፤

# የቀጠለ

**(7)“ተከታታይ የሙያ ማሻሻያ /ተሙማ/”** መምህራንና የትምህርት ቤት አመራሮች በማስተማር ወይም በትምህርት ቤት አመራርነት ስራ ላይ እስካሉ ድረስ ፍላጎትን መሰረት ባደረገና ከሚያስተምሩት ትምህርት ይዘት ወይም የማስተማር ስነ-ዘዴ ወይም የመማር ማስተማር መሪ ይዘቶችን መሠረት ያደረገ ትምህርት ቤት ተኮር ስልጠና ማለት ነው፤

**(8)“የህክምና ማስረጃ”** ማለት የህክምና አገልግሎት ከተገኘ በኋላ የህክምና አገልግሎቱ ከተሠጠበት የጤና ድርጅት የሚሰጥ የጤና ሁኔታ መግለጫ የምስክር ወረቀት ነው፤

**(9)“ወመህ”** ማለት በትምህርት ቤት ደረጃ ትምህርትን እንዲመራ የተሰየመ የወላጅ፣ መምህራን ህብረት ማለት ነው፤

**(10) “ቀትስቦ”** ማለት በቀበሌ ደረጃ ትምህርትን እንዲመራ የተሰየመ የቀበሌ ትምህርትና ስልጠና ቦርድ ማለት ነው፤

**(11)“የዲሲፕሊን ኮሚቴ”** ማለት የመምህራንንና የትምህርት ቤት አመራሮችን የዲሲፕሊን ጉዳዮች ለማየት የተቋቋመ አካል ነው፤

# የቀጠለ

**(12)“ የዲሲፕሊን ጉድለት” ማለት በመንግስት ሠራተኞች አዋጅ፣ በዚህ መመሪያ እና በሌሎች አግባብነት ባላቸው መመሪያዎች ላይ የተጠቀሱትን ግዴታዎች አለማክበር ነው፤**

(13) **“ሰው”** ማለት ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

(14)በዚህ መመሪያ በወንድ ጾታ የገለጸው የሴትንም ጾታ ያካትታል፤

## 3. የተፈጻሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ በቢሮውና በስሩ በሚገኙ ዞን ትምህርት መምሪያ፣ ብሔረ-ሰብ አስተዳደር ትምህርት መምሪያ፣ ሪጂዮ-ፖሊታን ትምህርት መምሪያ፣ከተማ አስተዳደር ትምህርት ጽህፈት ቤት፣ ወረዳ ትምህርት ጽህፈት ቤት፣ ክፍለ ከተማ ትምህርት ጽ/ቤት አንዲሁም ከቅድመ አንደኛ ደረጃ እስከ ሁለተኛ ደረጃ ባሉ የመንግስት ትምህርት ቤቶች ባሉ መምህራንና የትምህርት ቤት አመራሮች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

# 4. የዲሲፕሊን ጉዳይ አወሳሰን መርሆዎች

(1) መምህራንና የትምህርት ቤት አመራሮች እርስ በእርሳቸው መከባበርን ፣ ግልጽ አሠራርን፣የጋራ መግባባትና መተባበር እንዲሰፍን በማድረግ የትምህርት ቤቱን ተልዕኮ ማሳካት፤

(2) መከላከል ላይ ትኩረት በማድረግ ጥፋትን መቀነስ፤

(3) መምህራንና የት/ቤቱ አመራሮች በታማኝነትና በቅንነት እንዲሰሩ ማድረግ፤

(4) መልካም የሥራ ባህልና ተነሳሽነት እንዲጎለብት ማድረግ፤

(5) የሚፈጠርን አለመግባባት በፍትሓዊነትና በብቃት መፍታት፤

(6) በበቂ እና በተዓማኒ ማስረጃ ላይ የተመሠረተ ውሳኔ ማስተላለፍ፤

(7) ከጥፋቱ ጋር ተመጣጣኝነት ያለው ውሳኔ መስጠት፤

(8) ተመሳሳይነት ላለው ጥፋት የሚሰጥ ውሳኔ ወጥና ተቀራራቢ እንዲሆን ማድረግ፤

(9) ቅሬታ የማቅረብ መብትን ማክበር፤

## 5. የዲሲፕሊን ቅጣት ዓላማ

የዲስፕሊን ቅጣት ዋና ዓላማ መምህራንና የትምህርት ቤት አመራሮች በፈጸሙት የዲስፕሊን ጉድለት ተፀፅተው በአመለካከትና በሥነ-ምግባር እንዲታረሙና ብቁ ሠራተኞች እንዲሆኑ ለማስቻል ወይም የማይታረሙ ሆነው ሲገኙ ከጥፋቱ ጋር ተመጣጣኝ የሆነ የእርምት እርምጃ መውሰድ ነው።

## 6. የዲሲፕሊን ጉዳይ የሚታይባቸው መምህራን እና የትምህርት ቤት አመራሮች መብትና ግዴታዎች፤

(1) በዲሲፕሊን የተከሰሰ መምህር ወይም የትምህርት ቤት አመራር መብት

1) የተከሰሰበትን ጉዳይ የማወቅ፤

2) አንድ መምህር ወይም የትምህርት ቤት አመራር ከሥራው ወይም ከስራ ሀላፊነት ከታገደ የሚታገድበትን ምክንያት እና የእግዱን የቆይታ ጊዜ በጽሁፍ የማግኘት ወይም እንዲገለጽለት የመጠየቅ፤

3) ውሳኔ ወይም እልባት ባላገኘ ዲሲፕሊን ክስ ማግኘት የሚገባውን ጥቅማጥቅም ያለማጣት፤

## የቀጠለ

4) በሚመለከተው ክፍል የተወሰነውን የዲሲፒሊን ክስ ውሳኔ በጽሁፍ የማግኘት፤

5) በውሳኔው ቅር ከተሰኘ ለሚመለከተው ክፍል ይግባኝ ማቅረብ /ይግባኝ መጠየቅ፤

6) በግል አመለካከትና እምነት ምክንያት ያለመወቀስና ያለመወንጀል መብት አላቸው፤

## የቀጠለ

## (2) በዲሲፕሊን የተከሰሰ መምህር ወይም የትምህርት ቤት አመራር ግዴታ

1)በመንግስትየወጡትን **አዋጆች፣ደንቦችና መመሪያዎች የማክበር ፣ የመፈጸም፤**

2) ለሚሰጠው የምስክርነትቃል ወይም ለሚፈጽመው ቅጣት ወይም ለሚወሰድበት የዲሲፕሊን እርምጃ ሲጠየቅ **በቂ መረጃና ማብራሪያ የማቅረብ፤**

3) የዲሲፕሊን ክስ መጥሪያ ከሚመለከተው ክፍል ሲደርሰው **በቀጠሮ ቀን የመገኘት፤**

4) ጥፋት ያጠፋ አካል ሲገኝ **የማጋለጥና አጥፊው የዲስፕሊን ክስ እንዲመሠረትበት የማድረግ፤**

# 7. ከስራና ደመወዝ አግዶ ስለማቆየት

በዲሲፕሊን ጥፋት የተጠረጠረ ወይም የተከሰሰ መምህር ወይም የትምህርት ቤት አመራርን ከሥራ አግዶ ማቆየት የሚቻለው፣

(1) ከተጠረጠረበት ጉዳይ ጋር አግባብነት ያላቸውን ማስረጃዎች በማበላሸት፣ በመደበቅ ወይም በማጥፋት ምርመራውን ያሰናክላልተብሎ ሲታመን፤

(2) በመንግሥት ሃብትና ንብረት ላይ ተጨማሪ ጉዳት ያደርሳል ፣ ወይም

(3) ከተከሰሰበት ጥፋት ክብደት አንጻር የሌሎችን ሠራተኞች ሞራል የሚነካ ወይም የተገልጋዩ ሕዝብ በመሥሪያ ቤቱ ላይ ሊኖረው የሚገባውን እምነት ያዛባል፣ወይም

(4) ተፈጸመ የሚባለው ጥፋት ከሥራ ያሰናብታል ተብሎ ሲገመት ነው፤

(5)በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እስከ 4 በተገለፀው መሠረት አንድ መምህር ወይም የትምህርት ቤት አመራር ከሥራና ከደመወዝ ታግዶ ሊቆይ የሚችለው ከአንድ ወር ለማይበልጥ ጊዜ ይሆናል፤

(6) በዚህ አንቀጽ በተራ ቁጥር 5 መሠረት ከሥራና ከደመወዝ ታግዶ እንዲቆይ የሚደረግ መምህር ወይም የትምህርት ቤት አመራር ከመደበኛ ሥራው ታግዶ የሚቆይበት ጊዜና ከስራ የታገደበት ምክንያት በመሥሪያ ቤቱ የበላይ ኃላፊ ወይም በተወካዩ በጽሑፍ እንዲገለጽለትና እንዲያውቀው ይደረጋል፤

(7)መምህሩ ወይም የትምህርት ቤት አመራሩ በተከሰሰበት የዲስፕሊን ጥፋት ምክንያት ከሥራ እንዲሰናበት ካልተወሰነበት በስተቀር በእግዱ ወቅት ሳይከፈለው የቀረው ደመወዝ ያለወለድ ይከፈለዋል፤

(8)በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 7 መሠረት መምህሩ ወይም የትምህርት ቤት አመራሩ ደመወዙ እንዲከፈለውና ወደ ሥራው እንዲመለስ ሳይደረግ የዕግዱ ጊዜ ካበቃ፤

# የቀጠለ

1) የመዘግየቱ ምክንያት የዲስፕሊን ክሱን የማጣራቱ ሂደት ውስብስብነት ያለው ከሆነ መምህሩ ወይም የትምህርት ቤት አመራሩ ግማሽ ደመወዙ እየተከፈለው፣ ወይም
2) ለመዘግየቱ ምክንያት የሆነው መምህሩ ወይም የትምህርት ቤት አመራሩ ራሱ ከሆነ ያለደመወዝ ክፍያ እግዱ እስከ አንድ ወር ድረስ እንዲራዘም የመምህሩ ጉዳይ በትምህርት ቤቱ ርዕሰ መምህር እንዲሁም የትምህርት ቤት አመራሮች በሪጂዮ ፖሊታን ከተማ ወይም በወረዳ ወይም ከተማ አስተዳደር ወይም በክፍለ-ከተማ ትምህርት ጽህፈት ቤት ኃላፊ ሊወስን ይችላል፤
3) ከሥራና ከደመወዝ ታግዶ የቆየ መምህር ወይም የትምህርት ቤት አመራር ከሥራ እንዲሰናበት ወይም ደመወዙ እንዲከፈለውና ወደ ሥራው እንዲመለስ ሳይደረግ መደበኛውም ሆነ የተራዘመው የዕግድ ጊዜ ከተጠናቀቀ የሥራና የደመወዝ እግዱ ተነስቶ የዲስፕሊን ክሱ መታየት ይቀጥላል፤ ሆኖም ለመዘግየቱ ምክንያት የሆኑ አካላት ተጠያቂ ይሆናሉ፤

**8. የመምህራንና የትምህርት ቤት አመራሮች የዲሲኘሊን ጥፋት የሚታይባቸውና ውሳኔ የሚሰጥባቸውደረጃዎች**

(1) በትምህርት ቤት ደረጃ

1) በትምህርት ቤት ደረጃ የሚታየውን የዲስኘሊን ጉዳይ የሚመለከተው አካል የትምህርት ቤቱ የዲሲፐሊን ኮሚቴ ሲሆን ጉዳዩን በደንብ ከመረመረ በኃላ የውሳኔ ሃሳብ ለርዕሰ መምህሩ ይቀርባል፤

2) በትምህርት ቤቱ የዲሲፐሊን ኮሚቴ ተጣርቶ የሚቀርበው የውሳኔ ሀሳብ በትምህርት ቤቱ ርዕሰ መምህር ይጸድቃል፤

3) በትምህርት ቤት ደረጃ የሚታየው የዲሲኘሊን ጉዳይ የመምህራን ብቻ ይሆናል፤

(2)የትምህርት ቤት የዲሲፕሊን ኮሚቴ አደረጃጀት ፤

1) የትምህርት ቤቱ ምክትል ርዕሰ መምህር ----------- ሠብሳቢ

2) 2)የትምህርት ቤቱ ወመህ ሠብሳቢ ..................ምክትል ሠብሳቢ፤

3) የትምህርት ቤቱ ወመህ ሁለት የወላጅ ተወካይ----------- አባል፤

4) ሁለት የመምህራን ማህበር አባላት/አንዷ ሴት/--------------አባል፤

5) አንድ መምህር የሆነ የወመህ አባል -------- አባልና ጸሃፊ፤

(3)የወረዳ ወይም የከተማ አስተዳደር ወይም የክፍለ ከተማ ወይም የሪጂዮ-ፖሊታን ከተማ የዲሲፕሊን ኮሚቴ አደረጃጀት

1) በወረዳ ወይም በከተማ አስተዳደር ወይም በክፍለ- ከተማ ወይም በሪጂዮ-ፖሊታን ከተማ ደረጃ የሚታየው የዲሲኘሊን ጉዳይ የትምህርት ቤት አመራሮች ነው፤

2) የዲሲፕሊን ጉዳዩ በወረዳው ወይም በከተማ አስተዳደሩ ወይም በክፍለ ከተማው ወይም በሪጂዮ-ፖሊታን ከተማው የመምህራንና የትምህርት ቤት አመራር ልማት ቡድን ተጣርቶ የኮሚቴው አባል ካልሆኑ የልማት ቡድኑ ባለሙያዎች መካከል በሚወከል አንድ ዓላማ ፈጻሚ ባለሙያ ክስ እንዲመሰረት ይደረጋል፤

3) ኮሚቴው የወረዳ ወይም የከተማ አስተዳደር ወይም የክፍለ ከተማ ወይም የሪጂዮ-ፖሊታን ከተማ የትምህርት ቤት አመራሮች የዲሲኘሊን ኮሚቴ በሚል ስያሜ የሚጠራ ሲሆን አደረጃጀቱም እንደሚከተለው ይሆናል፤-

(1)የወረዳ ወይም የከተማ አስተዳደር ወይም የሪጂዮ-ፖሊታን ወይም የክፈለ-ከተማ ትምህርት ጽህፈት ቤት ወይም ትምህርት መምሪያ ምክትል ኃላፊ.....ሰብሳቢ፤

(2) የወረዳ ወይም የከተማ አስተዳደር ወይም የሪጂዮ-ፖሊታን ወይም የክፍለ ከተማ ትምህርት ጽህፈት ቤት ወይም ትምህርት መምሪያ መምህራንና ትምህርት ቤት አመራር ልማት ቡድን አንድ ባለሙያ ......አባል፤

(3) የወረዳ መምህራን ማህበር ሁለት ተወካዩች/አንዷ ሴት /.....አባል፤

(4) የወረዳ መምህራን ልማት ቡድን መሪ/ቡድን መሪ በሌለበት ተወካይ/........አባልና ፀሐፊ፤

## 9. የዲሲፕሊን ኮሚቴ አባላትን ስለመቀየር ፤

(1) ማንኛውም የዲሲፕሊን ኮሚቴ አባል እራሱን ከጉዳዩ በማግለልና ሌላን አባል ለማስጠላት ከባለጉዳዩ ጋር እየተገናኘ ምስጢር ያወጣ ወይም ቃለ ጉባኤዎችን ፣ መረጃዎችንና ጽሑፎችን ለባለጉዳዩ ያሳየ ወይም የተናገረ ወይም የሰጠ ከሆነ ፤

(2) የዲሲፕሊን ኮሚቴ አባል ክስ ከተመሠረተበት ሠራተኛ ጋር ጠብ ያለው ወይም እስከ ሦስት ደረጃ የስጋ ወይም የጋብቻ ዝምድና ያለው መሆኑ በማስረጃ ሲረጋገጥ ጉዳዩ በትምህርት ቤት ደረጃ የሚታይ ከሆነ በትምህርት ቤቱ ርዕሰ መምህር አማካኝነት ከኮሚቴ አባልነቱ እንዲነሳ ይደረጋል።ጉዳዩ የሚታየው በወረዳወይም በከተማ አስተዳደር ወይም በክፍለ -ከተማ ወይም በሪጂዮ -ፖሊታን ከተማ ደረጃ ከሆነ በጽህፈት ቤት ኃላፊው አማካኝነት ከኮሚቴ አባልነቱ እንዲነሳ ይደረጋል፤

(3) የትምህርት ቤቱ ርዕሰ መምህር ወይም የወረዳ ትምህርት ጽህፈት ቤት ኃላፊው የኮሚቴ አባሉን ለማንሳት የሚያስችል ማስረጃ ሳይኖረው ሲቀርና ማስረጃው በሚመለከተው የዲስኘሊን ኮሚቴ አባል ብቻ የሚታወቅ ከሆነ ጉዳዩን ላለማየት የዲሲኘሊን ኮሚቴ አባሉ ራሱን ከኮሚቴ አባልነት እንዲነሳ ጥያቄውን ማቅረብ አለበት፤

(4) በዚህ አንቀጽ ተራ ቁጥር 3 የተገለጸውን በመተላለፍ አባሉ በአባልነቱ ቀጥሎ የተገኘና ተገቢ ያልሆነ ውሳኔ እንዲወሰን መደረጉ ከተረጋገጠ አግባብ ባለው ሕግ የሚጠየቅ ይሆናል፤

## 10. የዲሲፕሊን ክስ ስለሚያቀርቡ አካላት

(1) ማንኛውም የትምህርት ተቋሙ ማህበረሰብ አባል የዲሲፕሊን መጓደል ተፈጽሞብኛል ብሎ ካመነ አሉኝ የሚላቸውን ማስረጃዎች በማቅረብ የዲሲፕሊን ክስ የማቅረብ መብት አለው፤

(2) በዚህ አንቀጽ ተራ ቁጥር 1 የተመለከተው አጠቃላይ አገላለጽ እንደተጠበቀ ሆኖ ግድፈቱ ወይም ጥፋቱ ተቋማዊ ሆኖ ሲገኝ፡-

1) በትምርት ቤት ደረጃ **በትምህርት ክፍል ተጠሪ** ወይም ርዕሰ መምህሩ በሚወክለው ሠራተኛ፤

2) በወረዳ ወይም በከተማ አስተዳደር ወይም በሪጂዮ-ፖሊታን ከተማ ወይም በክፍለ- ከተማ ደረጃ ከጽህፈት ቤቱ **የመምህራን ልማት ቡድን የኮሚቴ አባል** ካልሆኑት ባለሙያዎች መካከል የጽህፈት ቤት ኃላፊው በሚወክለው ሰው ክስ ሊመሰረት ይችላል፤

## 11.የዲሲኘሊን ኮሚቴ  ተግባርና ሃላፊነት

1) የዲሲኘሊን ጉዳይ የሚመለከቱ አካላት የተሰጣቸውን ተግባር በሚያከናውኑበት ጊዜ የሚያስፈልጉትን ማህደሮች ፣ መረጃዎችና ሰነዶች አስቀርበው የማየትና አግባብ ያለውን ሰው መጥራትና መጠየቅ ይችላሉ ።

2) የዲሲኘሊን ኮሚቴ  የቀረበለትን የዲሲፕሊን ክስ በሚያጣራበት ጊዜ፡-

(1)የመምህሩ ወይም የትምህርት ቤት አመራሩ ሙሉ ስም ከነ አያቱ፤

(2) መምህሩ ወይም የትምህርት ቤት አመራሩ   የተከሰሰበትን ጭብጥ፤

(3) ክሱን ያረጋግጣሉ ተብለው የቀረቡትን የጽሑፍም ሆነ የሰው ማስረጃዎች፤

(4) የመምህሩን ወይም የትምህርት ቤት አመራሩን የግል ማህደር፤

(5)  ስለቀረበው ክስ አግባብነት ያላቸውን ደንቦችና መመሪያዎች፤

(5) መምህሩ ወይም የትምህርት ቤት አመራሩ የሚያቀርባቸውን የጹሁፍና የሰው ማስረጃዎች፤

(7) ከላይ ከተመለከቱት ውጭ ሌሎች አግባብነት አላቸው ብሎ የሚገምታቸውን ማስረጃዎች የመመዝገብና የማገናዘብ ግዴታ አለበት፤

3) ክርክሩ የሚመራበት ሥርዓት፤

(1) ለተከሰሰው መምህር ወይም የትምህርት ቤት አመራር ክሱንና ማስረጃውን በወቅቱ በጹሑፍ እንዲደርሰውና የመከላከያ መልሱን በተሰጠው ጊዜ በጽሁፍ የማቅረብ መብቱ እንዲጠበቅለት፤

(2) የከሳሹ ምስክሮች ሲቀርቡ ተከሳሹ በተገኘበት ቃላቸውን እንዲሰጡና ተከሳሹም የሚፈልገውን የመስቀለኛ ጥያቄ እንዲያቀርብ እንዲሁም የተከሳሽ መከላከያ ማስረጃ በሚሰማበት ጊዜ ከሳሽ ተገኝቶ የመጠየቅ መብቱ እንዲጠበቅለት፤

(3) ተከሳሹ ክሱን የማዳመጥ የመከራከርና በክሱም የመከላከያ ማስረጃዎችንና ምስክሮችን የማቅረብ መብት ተጠብቆለት ክሱ በማስረጃ እንዲጣራ፣

(4) ከሳሽ ያቀረባቸው ማስረጃዎች ለተከሳሽ፣ ተከሳሽ ያቀረባቸው ለከሳሽ እንዲደርሳቸው የሚያደርግ ይሆናል፤

4) የዲሲፕሊን ኮሚቴው ሥራዎችን በሚያከናውንበት ጊዜ በተደጋጋሚ ሁኔታ ከሚያጋጥሙት የዲሲፕሊን ጉድለቶች በመነሳት አጠቃላይ ጥናት እያደረገ ለዲሲፕሊን አለመከበር መንስኤ የሚሆኑ ክስተቶች ሊወገዱ የሚችሉበትን የመፍትሄ አስተያየት ለትምህርት ቤቱ ርዕሰ መምህር ወይም ለወረዳ፣ ለከተማ አስተዳደር፣ ለክፍለ-ከተማ ትምህርት ጽህፈት ቤት ወይም ለሪጂ-ፖሊታን ከተማ ትምህርት መምሪያ ያቀርባል፤

## 12. የዲሲኘሊን ኮሚቴ ፀሀፊ ተግባርና ሃላፊነት

የኮሚቴው ጸሃፊ የሚከተሉትን ተግባራት ያከናውናል

(1) የዕለታዊ አጀንዳ ቅደም ተከተሉን ያዘጋጃል፤

(2) የስብሰባው ቃለ ጉባኤ በትክክል እየተፃፈና እየተዘጋጀ አባላቱም እየፈረሙበት በጥንቃቄ እንዲያዝ ያደርጋል፤

(3) ከሳሽና ተከሳሽ የሚሰጡት ቃል በትክክልና በጥንቃቄ እንዲመዘገብና ቃል ሰጪዎቹ እንዲፈርሙበት ያደርጋል፤

(4) በሁለቱም ወገን የሚቀርቡት ማስረጃዎች ተመዝግበውና ለኮሚቴው ቀርበው ከታዩ በኋላ በጥንቃቄ እንዲቀመጡ ያደርጋል፤

(5) ለተከሳሹ፣ ለምስክሮችና ለሌሎች አስረጅ የሚሰጡት መጥሪያዎች እንዲሁም ልዩ ልዩ ደብዳቤዎች እየተዘጋጁና ፊርማ እየተፈረመባቸው ለሚመለከተው ሰው ወይም መስሪያ ቤት መላካቸው ወይም መድረሳቸው እንዲረጋገጥ ማድረግ ይጠበቅበታል፤

13. <u>**በተከሳሽ በኩል ለኮሚቴው ስለሚቀርቡ የሰውና የጽሑፍ ማስረጃዎች፤**</u>

(1) ተከሳሹ ለተመሠረተበት ጥፋት ማፍረሻ ወይም መከላከያ የሚሆነውን ተፈቅዶ በስራ ላይ የነበረ መመሪያ ወይም የአሠራር ደንብ ወይንም ምስክሮች ማቅረብ አለበት፤

(2) ተከሳሹ እንዲቀርቡለት ወይም ግልባጭ እንዲሰጠው የጠየቃቸው ማስረጃዎች አዋጆች፣ ደንቦች እንደሁም መመሪያዎች በመስሪያ ቤቱ ውስጥ የሚገኙ ከሆነ ትምህርት ቤቱን ወይም ወረዳውን ወይም ከተማ አስተዳደሩን ወይም ክፍለ-ከተማውን ወይም ሪጂዮ-ፖሊታን ከተማ ትምህርት መምሪያውን መጠየቅ ይችላል፡፡ ትምህርት ቤቱ፣ወረዳው/ከተማ አስተዳደሩ ትክክለኛ ግልባጩን የመስጠት ግዴታ አለበት፤

# 14. <u>የዲሲኘሊን ቅጣት ዓይነቶች ፤</u>

(1)በተሻሻለው የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ሠራተኞች አዋጅ ቁጥር 253/2010 መሰረት የዲሲኘሊን ጉድለት የፈፀመ መምህር ወይም የትምህርት ቤት አመራር እንደጥፋቱ ክብደት ከሚከተሉት ቅጣቶች አንዱ ሊወሰንበት ይችላል፤

(2)ቀላል የዲሲፕሊን ቅጣት አይነቶች፤

1) የቃል ማስጠንቀቂያ፤
2) የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ፤
3) እስከ 15 ቀን  የሚደርስ የደመወዝ ቅጣት፤

## (2) ከባድ የዲሲፕሊን ቅጣት አይነቶች፤

1) እስከ ሦስት ወር የሚደርስ የደመወዝ መቀጫ፤

2) እስከ ሁለት ዓመት ለሚደርስ ጊዜ ከሥራ ደረጃ እና ከደመወዝ ዝቅ ማድረግ፤

3) ከሥራ ማሰናበት፤

**15. ቀለል  የዲሲፕሊን ቅጣት የሚያስከትሉ ጥፋቶች፤-**

**(1) መምህራንን ለቀለል የዲሲፕሊን ቅጣት የሚዳርጉ ጥፋቶች፤**

1) በትምህርት ቤት መለበስ ከሚገባው አለባበስ ውጭ  መልበስ ማለትም፡-

(1)  ሀይማኖታዊ የሆነ አለባበስ መልበስ፤

(2)  አካልን ለወሲብ ስሜት በሚያነሳሳ መልኩ አጋልጦ መልበስ፤

(3) ወሲብ ቀስቃሽና ጾታን የሚያንቋሽሽ ሥዕል ያለበትን ልብስ መልበስ፤

(4)  ያለውን ልብስ በንጽህና ጠብቆ አለመልበስ፤

( 5) የተማሪዎችን የመማር ሂደት ሊያደናቅፍ የሚችል ማንኛውም አለባበስ፤

2) በተማሪዎች ወይም በመምህራን ወይም በድጋፍ ሰጪ ባለሙያዎች  ወይም በትምህርት ቤት አመራሮች ላይ ጸያፍ ቃላትን መጠቀም፤

3) ለቅርብ ተጠሪ ሳያሳውቁ ወይም ፈቃድ ሳይኖረው ከፍል ውስጥ አለመግባት፣በክፍል ውስጥ ምልከታ በስብሰባዎች፣ በቤተሙከራ ተግባራት ወዘተ አለመሳተፍ፤

4) በትምህርት ቤት ግቢ ውስጥ እያሉ ክፍለ ጊዜ የሚሸራርፉ(ሠዓት ሳይደርስ ከክፍል ቀድሞ የሚወጡ ወይም  ዘግይቶ አለመገባት፤

5) በተመደበበት ክፍል ተማሪዎችን በየዕለቱ ስም በመጥራት አቴንዳንስ አለመያዝ፤

6) የተማሪዎችን ፈተና በተቀመጠው የጊዜ ገደብ አርሞ ውጤትን  በማያሳወቅ መምህር ላይ ተመጣጣኝ ቅጣት ፤ አለማሳወቅ

7) በሰንደቅ አላማ አከባበር ሥነ-ሥርዓት አለመሳተፍ፣ተማሪዎች እንዲሠለፉ አለማድረግ፤

8) ለተማሪዎች ተገቢውን የምክር አገልግሎት አለመስጠት፤

## (2) የትምህርት ቤት አመራሮችን ለቀላል የዲሲፕሊን ቅጣት የሚዳርጉ ጥፋቶች

1) በተማሪዎች ወይም በመምህራን ወይም በድጋፍ ሰጪ ባለሙያዎች ላይ ጸያፍ ቃላትን መጠቀም፤

2) የመምህራንና የአስተዳደር ሠራተኞችን የሥራ ድርሻ አለማሳወቅ፤ ኃላፊነታቸውን በብቃት እንዲወጡ ከአዳዲስ ግኝቶችና የመማር ማስተማር ሥነ ዘዴዎች ጋር እንዲተዋወቁ አለማድረግ፤

3)የተማሪዎችን አዕምሯዊ፣ አካላዊና ስሜታዊ ባህርይን ለፈጠራና ለችግር ፈቺነት፣ ለሥራ ወዳድነትና ለመልካም ሥነ-ምግባርና ለአገራዊ አንድነት የሚያበቃ የመማር ማስተማር ሂደትን እንዲኖር አለማድረግ፤

4) የመምህራን ዝውውርና የደረጃ እድገት ወቅቱን ጠብቆ እንዲካሄድ ተገቢውን መረጃ በማጠናቀር ለሚመለከተው አካል አለመላክ፤

5)የትምህርት ቤቱን ልዩ-ልዩ ኮሚቴዎች በመመሪያው መሠረት አለማቋቋም፤ ተግባርና ሃላፊነታቸውንም እንዲወጡ አለማድረግ፤

6) በትምህርት ቤት ግቢ ውስጥ መለበስ ከሚገባው አለባበስ ውጭ መልበስ ወይም በለበሱ የትምህርትቤቱ መምህራንና አስተዳደር ሠራተኞች ላይ ማስተካከያ አለመውሰድ፤

7) የሠንደቅ አላማ አከባበር ስነ-ሥርዓት ተግባራዊ እንዲሆን አለመከታተል፤

8)ከጉድኝት ሱፐርቫይዘር እና ከወረዳ ትምህርት ጽህፈት ቤት የሚሰጠውን ተጨማሪ ተግባራት ለማከናወን ፈቃደኛ አለመሆን፤

**16. ከባድ የዲሲኘሊን ቅጣት የሚያስከትሉ ጥፋቶች፤**

**(1) መምህራንን ለከባድ የዲሲፐሊን ቅጣት የሚዳርጉ ጉዳዮች**

1) ትዕዛዝ ካለማክበር ፣ ከመለገም ወይ ከቸልተኝነት በመነጨ በስራ ላይ በደል ከደረሰ ፤

2) በትምህርት ቤት ግቢ ውስጥ እያሉ ክፍለ ጊዜ መሸራረፍ(ሠዓት ሳይደርስ ከክፍል ቀድሞ መውጣት ዘግይቶ ወደ ክፍል መግባት)፤

3) ዕለታዊ ፣ሳምንታዊ እና ዓመታዊ የትምህርት እቅድን በተቀመጠው የጊዜ ሰሌዳ እየሰሩ አለማቅረብና በክፍል ውስጥ አለመጠቀም፤

4) በትምህርት ቤት ደረጃ በሚተገበረው የመርሱ ተከታታይ  የሙያ ማሻሻያ (ተሙማ) ፕሮግራም አለመሳተፍ ወይም ለፕሮግራሙ አደናቃፊ ተግባራትን መፈጸም ወይም ፕሮግራሙ በትምህርት ቤቱ ውጤታማ እንዲሆን ስልት ቀይሶ አለመንቀሳቀስ፤

5) በሚመድቡበት የተሙማ አስተባባሪነት ወይም አማካሪነት አለመሳተፍ ወይም ለመሳተፍ ፈቃደኛ አለመሆን ፤

6) ሳምንታዊ የተሙማ ፖርት ፎሊዮ አለማደራጀት፤

7) ወደ ትምህርት ቤት የመጡ ተማሪዎች ሳያቋርጡና ክፍል ሳይደግሙ ትምህርታቸውን እንዲጨርሱ  ስልት በመቀየስ የትምህርት ብክነትን መቀነስ አለመቻል፤

8) የተማሪዎችን ፈተና በተቀመጠው የጊዜ ገደብ አርሞ ውጤትን አለማሳወቅ፤

9) የመማር ማስተማር ስራው በአግባቡ እንዳይካሄድ ሆነ ብሉ ማወክ ወይም ከሚያውኩት ጋር መተባበር ፤

10) በቀላል የዲሲኘሊን ቅጣት እርምጃዎች ባለመታረም ያለ በቂ ምክንያት በተደጋጋሚ ከስራ መቅረት ወይም የሥራ ሰዓት አለማክበር ፤

11) በትምህርት ቤት ግቢ ውስጥ  በጠብ አጫሪነት መደባደብ ፤

12) በስካር ወይም በአደንዛዥ ዕጽ ሱስ በመመረዝ ስራን መበደል ወይም ለተማሪዎች መጥፎ ተምሳሌት መሆን፤

13) ለተማሪዎች ያለአግባብ ውጤት መጨመር ወይም የፈተናን ሚስጥራዊነት አመለጠበቅ ወይም በፈተና ሠዓት ተማሪዎች እንዲኮራረጁ ማድረግ ወይም ጉቦ መቀበል ወይም ጉቦ እንዲሰጠው መጠየቅ፤

14) ስራን የመበደል፣ እምነት የማጉደል ወይም የሥነ-ምግባር ችግር ወይም የንብረትና ገንዘብ ማጉደል ከታየባቸው፤

15 በስራ ቦታ ለህዝብ ሞራል ተቃራኒ የሆነ ድርጊት መፈጸም፤

የቀጠለ------

16) የሌብነት፣ የእምነት ማጉደል፣ የሃሰት ማስረጃ ማቅረብ፣ የማታለል ወይም የማጭበርበር ድርጊት መፈፀም፤

17)ተደጋጋሚ እገዛ እና የአቅም ግንባታ ስራ ተደርጎለት የብቃት ማነስ የሚታይበት ከሆነ፤

18) መምህራንና የትምህርት ቤት አመራሮች ሃላፊነትን/ ስልጣንን አላግባብ መጠቀም፤

19) በስራ ቦታ ላይ ፆታዊ ትንኮሳ ወይም ጥቃት እንዳይፈጸም የበኩሉን አስተዋጽኦ ካላበረከተ፤

20) ከዚህ በላይ ከተዘረዘሩት ጋር ተመሳሳይ ክብደት ያለው ሌላ የዲሲኘሊን ጉድለት መፈፀም፤

## (ለ) የትምህርት ቤት አመራሮችን ለከባድ የዲስፕሊን ቅጣት የሚዳርጉ ጥፋቶች

1)የሌብነት ወይም የእምነት ማጉደል ወይም  የሃሰት ማስረጃ ማቅረብ ወይም የማታለል ወይም የማጭበርበር ድርጊት መፈፀም፤

2)በትምህርት ቤት ደረጃ በሚተገበረው **የመርሱ ተከታታይ  የሙያ ማሻሻያ (ተሙማ)** ፕሮግራም አለመሳተፍ ወይም ለፕሮግራሙ አደናቃፊ ተግባራትን መፈጸም ወይም ፕሮግራሙ በትምህርት ቤቱ ውጤታማ እንዲሆን ስልት ቀይሶ አለመንቀሳቀስ፤

3) በጉድኝቱ በታቀፉ ትምህርት ቤቶች የሚገኙ ነባርና ጀማሪ **መምህራን በተከታታይ የሙያ ማሻሻያ ፕሮግራም** እንዲሳተፉ የተለያዩ ስልቶችን በመጠቀም ፕሮግራሙ ውጤታማ እንዲሆን አለማድረግ ፤

4) ሳምንታዊ የተሙማ ፖርት ፎሊዮ አለማደራጀት፤

5) በቀላል የዲሲኘሊን ቅጣት እርምጃዎች ባለመታረም ያለ በቂ ምክንያት በተደጋጋሚ **ከስራ መቅረት ወይም የስራ ሰዓት አለማክበር፤**

## የቀጠለ

6)በስካር ወይም በአደንዛዥ ዕጽ ሱስ በመመረዝ ስራን መበደል ወይም ለተማሪዎች መጥፎ ተምሳሌት መሆን፤

7) **ደረጃ አንድ እና ደረጃ ሁለት የሆኑ ትምህርት ቤቶች** በኢንስፔክሽን ግምገማ ከተሰጠው የኢንስፔክሽን ደረጃ ወደሚቀጥለው ደረጃ ማሳደግ አለመቻል፤

8)በትምህርት ቤቱ ወይም በጉድኝት ማዕከሉ ንብረት ላይ ሆን ብሎ ወይም በቸልተኝነት ጉዳት ማድረስ፤

9)በጉድኝት ማዕከሉ በሚገኙ ትምህርት ቤቶች **ምርጥ ተሞክሮዎችን በመቀመር** ወደ ሌሎች እንዲሰፋ ማድረግ አለመቻል፤

10) በስራ ቦታ ላይ ፆታዊ ትንኮሳ ወይም ጥቃት መፈፀም፤

# የቀጠለ

11)ወላጆቹን በእቅዱ መሰረት ትምህርት ቤት እንዲገኙ በማድረግ በትምህርት ስራ ላይ ውይይት እንዲያደርጉ በማድረግ የትምህርት ቤቱን ችግር መቅረፍ አለመቻል፤

12) የፈተናን ሚስጥራዊነት አለመጠበቅ ወይም **በፈተና ሠዓት ተማሪዎች እንዲኮራረጁ** ማድረግ ወይም ፈተና በመምህራን ተሰርቶ ለተማሪ እንዲደርስ ማድረግ፤

13)ተደጋጋሚ እገዛ እና የአቅም ግንባታ ስራ ተደርጎለት የብቃት ማነስ የሚታይበት ከሆነ፤

14)የመማር-ማስተማሩን ሥራ በቅርብ በመከታተል በየጊዜው የክፍል ውስጥ ምልከታ በማድረግ ጉድለት በሚታይባቸው ጉዳዮች ላይ አስፈላጊውን የእርምት እርምጃ ካልወሰደ፣ ለመምህራንም እገዛ ካላደረገ፤

15)የትምህርት ቤቱ ሀብትና ንብረት በአግባቡ መጠበቁንና በትክክል በሥራ ላይ መዋሉን ክትትል ካላደረገ፤

## የቀጠለ

16) ለትምህርት የታቀዱ ቀኖች ያለብክነት በሥራ ላይ እንዲውሉ አለማድረግ፣ ከአቅም በላይ በሆነ ሁኔታ የባከነ ካለም ማካካሻ እንዲሰጥ ካላደረገ፤

17) በአቅድ የተሰጠውን የተማሪ ምዝገባ አለማሳካት፣የትምህርት ብክነትን መቀነስ አለመቻልና የተማሪዎችን ከክፍል ክፍል ሽግግር በውጤታማነት አለመፈጸም፤

18) ተዓማኒ እና ወቅታዊ የሆኑ ልዩ-ልዩ መረጃዎችን በጥራት በማደራጀት ለሚመለከታቸው ክፍሎች አለመላክ፤

19) በስራ ቦታ ላይ ፆታዊ ትንኮሳ ወይም ጥቃት እንዳይፈጸም የበኩሉን አስተዋጽኦ ካላበረከተ፤

## 17. በዲሲኘሊን ውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ከግል ማህደር ስለሚወሰዱ ማስረጃዎች አጠቃቀም፤

(1)የዲሲፕሊን ክስ የቀረበበት መምህር ወይም የትምህርትቤት አመራር ያሳየው መልካም ጠባይና አጥጋቢ የስራ አፈፃፀም ወይም በተቃራኒ የነበረውን መጥፎ ፀባይና ደካማ የስራ አፈፃፀም ለመገምገም የቀረበበትን ክስ አጣርቶ ሚዛናዊ ውሳኔ ለመስጠት አስፈላጊ የሆነውን ማስረጃ ከሚመለከተው አካል አስቀርቦ መመልከት ይችላል፤

(2)በተከሳሽ መምህር ወይም የትምህርት ቤት አመራር ላይ በተለይ ከባድ የዲሲኘሊን እርምጃ ሊያስወስንበት የሚችል ሲሆን ባለፈው የአገልግሎት ዘመን ስላስገኘው አጥጋቢ የስራ አፈፃፀም ውጤት ከቅርብ ተጠሪው በጊዜው በጹሑፍ የተሰጠውን አስተማማኝ ማስረጃ ኮሚቴው ከአዲሱ ክስ ጭብጥ ጋር በማገናዘብ ለቅጣት ማቅለያ ሊጠቀምበት ይችላል፤

# የቀጠለ

(3) በወቅቱ በጽሑፍ ያልተገለፀለት ቅጣት ከግል ማህደሩ ጋር ተያይዞ እንዲገኝ በመደረጉ ብቻ በሪከርድ የተመዘገበ ቅጣት ሆኖ ሊቆጠርና ከግምት ውስጥ ሊገባ አይችልም፤

(4)አንድ መምህር ወይም የትምህርት ቤት አመራር  በዲስፕሊን ከተቀጣ በኋላ **ቅጣቱ በሪከርድነት ሊቆይና ሊጠቀስበት** የሚችለው፣

1) ቀላል የዲስፕሊን ቅጣት ከሆነ ቅጣቱ ከተወሰነበት ቀን ጀምሮ **ለአንድ ዓመት፣**

2) ከባድ የዲስፕሊን ቅጣት ከሆነ ቅጣቱ ከተወሰነበት ቀን ጀምሮ **ለሁለት ዓመት የሚቆይ ይሆናል፤**

(5) ቀላል የዲሲፕሊን ቅጣት የተቀጣ መምህራን ወይም የትምህርት ቤት አመራር ውሳኔው ከተወሰነበት ቀን ጀምሮ አንድ ዓመት ካለፈ በኋላ በደረጃ እድገት ውድድር ላይ ተሳታፊ እንዲሆን ይደረጋል፣ የቅጣት ሪከርዱም ቅጣቱ በተወሰነበት መምህር ወይም የትምህርት ቤት አመራር ጠያቂነት እንዲነሳ ይደረጋል፤

(6)ከባድ የዲሲፕሊን ቅጣት የተቀጣ መምህር ወይም የትምህርት ቤት አመራር ውሳኔው ከተወሰነበት ቀን ጀምሮ ሁለት ዓመት ካለፈ በኋላ በደረጃ እድገት ውድድሩ ላይ ተሳታፊ እንዲሆን ይደረጋል፣ የቅጣት ሪከርዱም ቅጣቱ በተወሰነበት መምህርና የትምህርት ቤት አመራር ጠያቂነት እንዲነሳ ይደረጋል፤

(7)የዲሲፕሊን ቅጣቱንና የደረጃ እድገት የመወዳደሪያ የጊዜ ገደቡን ያጠናቀቀ መምህር ወይም የትምህርት ቤት አመራር በደረጃ እድገት የሚቀርበው የደረጃ እድገት የሚፈፀምበትን ወቅት ጠብቆ ይሆናል፤ ይሁንና የዲሲፕሊን ውሳኔ ከመሰጠቱ በፊት የነበረ የውጤት ተኮር ነጥብና የቆይታ ጊዜ ካለ ቅጣቱን ካጠናቀቀ በኋላ በሚኖረው አገልግሎት ላይ ተደምሮ ለደረጃ እድገት ሊያወዳድረው ይችላል፤

(8) የዲሲፕሊን ቅጣት የተወሰነበት መምህር ወይም የትምህርት ቤት አመራር የቅጣቱ አይነት በሶስት ወር ደመወዝ የተወሰነ ቅጣት ከሆነ ከወር ደመወዙ 1/3 /አንድ ሶስተኛ/እየተከፈለ ወይም ቅጣቱ ከ1 ወር ደመወዝ በታች ሆኖ በወር ደመወዙ ከ1/3 የሚሸፈን ካልሆነ ከተከታታይ ወር ደመወዝ ተግባራዊ ሆኖ ቅጣቱ እንዲጠናቀቅ ይደረጋል፤

(9) የዲሲፕሊን ቅጣት የተወሰነበት መምህር ወይም የትምህርትቤት አመራር የሪከርድ ጥፋት እንዳይጠቀስበት ለርዕሰ መምህሩ ወይም ለወረዳ ወይም ለክፍለ ከተማው ወይም ለከተማ አሰተዳደሩ ትምህርት ጽህፈት ቤት ሃላፊ ወይም ለሪጂዮ ፖሊታን ከተማ ትምህርት መምሪያ ኃላፊ ጥያቄ ማቅረብ የሚችለው በዚህ አንቀጽ በተራ ቁጥር 5 እና 6 የተመለከተው **የማቆያ ጊዜ ገደብ** ከተጠናቀቀ በኋላ ነው፤

## 18. የማስረጃዎች ወጪና ሚስጥር አጠባበቅ፤

(1) የማስረጃዎች አቀራረብ የገንዘብ ወጪ የሚያስከትል ከሆነ ተከሳሹ ለሚያቀርበው ማስረጃ የሚያስፈልገውን ወጪ ራሱ ይችላል፤

(2) የዲሲፕሊን ኮሚቴ የውሳኔ አስተያየት በርዕሰ መምህሩ ወይም በወረዳ ወይም በክፍለ-ከተማው ወይም በከተማ አስተዳደሩ ትምህርት ጽህፈት ቤት ኃላፊ ወይም በሪጂዮ-ፖሊታን ከተማ ትምህርት መምሪያ ኃላፊ ፀድቆ በጽሑፍ ለባለጉዳዩ እስኪገለጽለት ድረስ ሚስጥር ሆኖ መጠበቅ አለበት፤

# 19. የቅሬታ አቀራረብ

## (ሀ) የመምህራን የቅሬታ አቀራረብ ሥነ-ስርዓት

1) የዲሲፕሊን ውሳኔ የተወሰነበት መምህር በትምህርት ቤቱ የዲሲፕሊን ኮሚቴ በተሰጠው ውሳኔ የማይስማማ ከሆነ ቅሬታውን **በሰባት ተከታታይ የስራ ቀናት** ለትምህርት ቤቱ ቀትስቦ ያቀርባል፤

2) የትምህርት ቤቱ ቀትስቦ በትምህርት ቤቱ ዲሲፕሊን ኮሚቴ በተሠጠው ውሳኔ ላይ የቀረበውን ቅሬታ መርምሮ **በሰባት ተከታታይ የስራ ቀናት ውሳኔ** ይሰጣል፤

3) ቀትስቦ በሰጠው ውሳኔ ላይ የማይስማማ ቅሬታ አቅራቢ በሰባት ተከታታይ የስራ ቀናት ለወረዳ ወይም ለከተማ አስተዳደር ወይም ለክፍለ-ከተማ ትምህርት ጽህፈት ቤት ወይም ለሪጂዮ-ፖሊታን ከተማው ትምህርት መምሪያ የዲሲፕሊን **ኮሚቴ ቅሬታውን ሊያቀርብ** ይችላል፤

የቀጠለ

(4) ከላይ በተራ ቁጥር 3 የተጠቀሰው የመምህራንና የትምህርት ቤት አመራሮች የዲሲፕሊን ኮሚቴ ቅሬታውን መርምሮ በሰባት ተከታታይ ቀናት ውስጥ ለቅሬታ አቅራቢው በጽሁፍ መልስ ይሠጣል፤

(5) በዲሲፕሊን ኮቴው በተሰጠው ውሳኔ ቅሬታ ያለው አካል ቅሬታውን ለወረዳ ወይም ለከተማ አስተዳደር ወይም ለክፍለ ከተማው ትምህርት ጽህፈት ቤት  ወይም ለሪጂዮ-ፖሊታን ከተማው ትምህርት መምሪያ ቤት ኃላፊ በአምስት ተከታታይ የስራ ቀናት አቅርቦ የመጨረሻ ውሳኔ ይሰጥበታል፤

(6) በኃላፊው በተሠጠው ውሳኔ የማይረካ መምህር ቅሬታውን በአምስት ተከታታይ የስራ ቀናት ውስጥ  ለወረዳ ወይም ለከተማ አስተዳደር ወይም ክፍለ-ከተማ ወይም ለሪጂዮ-ፖሊታን ከተማ ሲቭል ሰርቪስ ቅሬታ ሰሚ ማቅረብ ይችላል ፤

## የቀጠለ

(7)የወረዳ ወይም የከተማ አስተዳደር ወይም የክፍለ-ከተማ ወይም የሪጂዮ-ፖሊታን ከተማ ሲቪል ሰርቪስ ቅሬታ ሰሚ አካል ጉዳዩን በጥልቀት መርምሮ ለትምህርት ጽህፈት ቤት ወይም ለትምህርት መምሪያው ኃለፊ በአምስት ቀናት ውስጥ የውሳኔ ሃሳብ ያቀርባል ፤

(8)የትምህርት ጽህፈት ቤት ወይም የትምህርት መምሪያ ኃላፊው የቀረበለትን የውሳኔ ሃሳብ መርምሮ በሶስት ተከታታይ ቀናት ውስጥ ውሳኔውን በፅሁፍ ያሳወቃል፤

(9)የጽህፈት ቤት ወይም የመምሪያ ኃላፊው በሰጠው የመጨረሻ ውሳኔ የማይረካ መምህር ቅሬታውን በክልሉ መንግስት ሰራተኞች አስተዳደር ፍርድ ቤት የቅሬታ አቀራረብ ሥነ-ስርዓት መሰረት ተፈጻሚ ይሆናል፤

## (ለ) የትምህርት ቤት አመራሮች የቅሬታ አቀራረብ ሥነ-ስርዓት

(1) የዲሲፕሊን ውሳኔ የተወሰነበት የትምህርት ቤት አመራር በወረዳ ወይም በከተማ አስተዳደር ወይም በክፍለ-ከተማ ትምህርት ጽህፈት ቤት ወይም በሪጂዮ-ፖሊታን ትምህርት መምሪያ በተሰጠው ውሳኔ የማይስማማ ከሆነ ቅሬታውን በሰባት ተከታታይ የስራ ቀናት ለኃላፊው ያቀርባል፤

(2) የዲሲፕሊን ውሳኔ የተወሰነበት የትምህርት ቤት አመራር በወረዳ ወይም በከተማ አስተዳደር ወይም በክፍለ-ከተማ ትምህርት ጽህፈት ቤት ወይም በሪጂዮ-ፖሊታን ከተማ ትምህርት መምሪያ በተሰጠው ውሳኔ የማይስማማ ከሆነ ቅሬታውን በሰባት ተከታታይ የስራ ቀናት ለወረዳው ወይም ለከተማ አስተዳደሩ ወይም ለክፍለ-ከተማው ቅሬታ ሰሚ በጽሁፍ ያቀርባል፤

የቀጠለ---

(3) የወረዳው ወይም የከተማ አስተዳደሩ ወይም የክፍለ-ከተማው ወይም የሪጂዮ-ፖሊታን ሲቪል ሰርቪስ መምሪያው ቅሬታ ሰሚ ጉዳዩን አጣርቶ በአምስት ተከታታይ ቀናት ውስጥ ለትምህርት ጽህፈት ቤት ኃላፊው የውሳኔ ሀሳብ ያቀርባል። ለወረዳው ወይም ለከተማ አስተዳደሩ ወይም ለክፍለ-ከተማው ቅሬታ ሰሚ በጽሁፍ ያቀርባል፤

(4) በወረዳወይም በከተማ አስተዳደር ወይም በክፍለ-ከተማ ደረጃ ወይም በሪጂዮ ፖሊታን ከተማ ደረጃ በተሰጠው ውሳኔ የማይስማማ የትምህርት ቤት አመራር በክልሉ መንግስት ሰራተኞች የቅሬታ አቀራረብ ስነ-ስርዓት መሰረት ተፈጻሚ ይሆናል።

## 20. የይርጋ ጊዜ

(1) ቀላል የዲስፕሊን ቅጣት የሚያስከትል ጥፋት የፈፀመ መምህር ወይም የትምህርት ቤት አመራር የፈጸመው ጥፋት ከታወቀበት ቀን ጀምሮ እስከ ስድስት ወር እርምጃ ካልተወሰደበት በዲስፕሊን ተጠያቂ አይሆንም፤ ሆኖም በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ እርምጃ ያልወሰደው የሥራ ኃላፊ ተጠያቂ ይሆናል።

(2) በወንጀል ጭምር የሚያስጠይቅ ከባድ የዲስፕሊን ቅጣት የሚያስከትል ጥፋት የፈጸመ መምህር ወይም የትምህርት ቤት አመራር የወንጀሉን ክስ ለማቅረብ በወንጀል ሕጉ በተቀመጠው የይርጋ ጊዜ ውስጥ በዲስፕሊን ካልተከሰሰ በጥፋቱ ተጠያቂ አይሆንም።

(3) በወንጀል የማያስጠይቅ ከባድ የዲስፕሊን ቅጣት የሚያስከትል ጥፋት የፈጸመ መምህር ወይም የትምህርት ቤት አመራር የደንብ መተላለፍ ክስን ለማቅረብ በወንጀል ሕጉ በተደነገገው የይርጋ ጊዜ ውስጥ በዲስፕሊን ካልተከሰሰ በጥፋቱ ተጠያቂ አይሆንም።

# የቀጠለ

(4) በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 እስከ 3 የተደነገጉት የዲስፕሊን ክስ ማቅረቢያ የይርጋ ጊዜያት ቢኖሩም የዲስፕሊን ክስ ለማቅረብ ኃላፊነት ያለበት የሚመለከተው የሥራ ኃላፊ ጥፋት መፈጸሙን ካወቀበት ቀን ጀምሮ በስድስት ወር ውስጥ ክሱን ካላቀረበ ተጠያቂ ይሆናል።

(5)ማንኛውም መምህር ወይም ትምህርት ቤት አመራር ከሥራ በመታገዱ ምክንያት ከእግዱጋር ያልተያያዙ ሌሎች መብቶቹንና ግዴታዎቹን ተፈጻሚነት አያስቀርም።

## ክፍል አምስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 21. ስለተሻሩ እና ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸው መመሪያዎችና አሠራሮች

1) የ2007 ዓ.ም የመምህራን፣የርዕሰ መምህራንና የሱፐርቫይዘሮች የዲሲፕሊን አፈጻጸም መመሪያ እና ማሻሻያ መመሪያዎች እና ደብዳቤዎች በዚህ መመሪያ ተተክቷል።

2) ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረኑ ሌሎች መመሪዎችና የተለመዱ አሠራሮች በዚህ መመሪያ በተመለከቱ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖራቸውም።

3) ክፍለ -ከተማዎች በሰው ሃይል ተደራጅተው የመምህራንን ምልመላ ፣መረጣ እና የስራ ስምሪት ማከናወን እስኪችሉ ድረስ የሪጂዮ-ፖሊታን ከተማዎች ስራውን ያከናውናሉ።

## 21. <u>መመሪያውን ስለማሻሻል</u>

ይህን መመሪያ ቢሮው እንደአስፈላጊነቱ ሊያሻሽለው ይችላል።

## 22. <u>መመሪያው ስለሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ መመሪያ ከ------------/2014 ዓ/ም ጀምሮ ተፈፃሚ ይሆናል።